<u>ትምህርት ነክ ጥያቄዎችና መልሶች ወይም አስተያየቶች</u>

በሀገራችን ትምህርትን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ችግሮች አሉ። ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ለመፈለግ የባለሙያዎች ተሳትፎ አስፈላጊ ነው። ይህን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም በትምህርት መስክ የተከሰቱትን ችግሮች ከመስክ በመሰብሰብና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም ሆነ ውጭ ካሉ ምሁራን አስተያየት በመጠየቅ ጥያቄዎቹን ከነመልሶቻቸው በዚህ ዓምድ ያወጣል።

ይሁን እንጂ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶች የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም ሳይሆኑ የመልስ ሰጪው ክፍል መሆናቸውን አስቀድመን እናስገነዝባለን።

በዚህ ዕትም ያወጣነው ዝግጅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የመንግሥትና የመንግሥት ካልሆኑ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ፣ ተቀዳሚ መምህራንና መምህራን የተገኙትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ነው። ለጥያቄዎቹም መልስ ወይም አስተያየት በመስጠት የተባበሩን በትምህርት ሚኒስቴር የሚገኙ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ናቸው።

1. ጥያቄ፣ ለአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች፣ ለምሳሌ ለአማርኛ ፣ እንግሊዝኛ ፣ ሒሳብ ወዘተ በሳምንት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ከትምህርቱ ይዘት ጋር ስለአለመመጣጠኑ፣ መምህራን ሁለት የትምህርት ዓይነቶችን በ/major/ እና /minor/ እንዲያስተምሩ ስለመደረጉ በዚህም የተነሳ መምህራን በቂ ዝግጅት ሊያደርጉ ስላለመቻላቸው ምን መፍትሔ ይኖራል?

<u>በት/ሚር ከሥርዓተ–ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የተገኘ መልስ</u>

የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍት ከ1984 ጀምሮ ከ9ኛ–12ኛ ክፍል ተሻሽለው ይቀርባሉ። በሒሳብ ትምህርት በኩል ያለውን የክፍለ ጊዜና የይዘት አለመጣጣም ለማስወገድ መምህራን መጽሐፍቱ ውስጥ የተሰጡትን ጥያቄዎች አንድ

በአንዱ መሥራት እንደሌለባቸው አውቀው የተወሰኑትንና ክፍል ውስጥ ቢሰሩ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል የሚሏቸውን ብቻ መርጠው በመሥራት የቀሩትን ለተማሪዎቻቸው የቤት ሥራ ወይም መልካቸውን ቀየር በማድረግ ለትናንሽ ፈተናዎች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ:: በዚህ ዘዴ ከተሠራ የተጠቀሰው ችግር ይፈታል የሚል አስተሳሰብ አለ::

<u>በት/ሚር ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ የተገኘ መልስ</u>

የክፍለ ጊዜው ድልድል ማነስ ከትምህርት ዓይነቶች መብዛትና ሁሉንም ትምህርቶች እስከተወሰነ የክፍል ደረጃ ድረስ ሁሉም ተማሪዎች እንዲማሩዋቸው ከመደረጉ የተነሣ የተፈጠረ ሲሆን ፣ ይዘትን በማሻሻል ረገድ ደግሞ አስተያየቶችን በመሰብሰብ የተሻሻሉ አሉ ፣ ወደፊትም የሚሻሻሉ ይኖራሉ:: አንዳንዱም ችግር መምህራኑ ለማስተማር በቂ ሥልጠና ስለሌላቸውና ፍላጎቱም ሆነ ዝግጅቱ ስለሚጎድላቸው መጽሐፉን በሙሉ እንዉጫው ከማለት የሚፈጠር ችግር ሊሆን ይችላል የሚል አስተሳሰብ አለ::

2. ጥያቄ፣ ለየትምህርት ዓይነቱ ስለሚዘጋጁ ሲለበሶች / syllabi / የማስተማሪያ መጽሐፍት ይዘት ፣ መልመጃዎችና ክፍለ ጊዜ ድልድል መምህራን አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋል ወይ ? ይህ ካልተደረገስ ለምን ?

<u>በት/ሚር ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ የተገኘ መልስ</u>

መምህራን በየሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ውስጥ ያለውን ችግር አስመልክተው አስተያየት ለመስጠት እንዲችሉ በየትምህርት ቤቱ የሥርዓተ ትምህርት ኮሚቴ ከሞላ ጎደል ተቋቁሟል:: በየትምህርት ክፍሎች / departments / የሚያጋጥሙ ችግሮች እየተሰባሰቡ በዚሁ ኮሚቴ እየተተቸባቸው ለዝግጅትና ለአስፈጻሚው ክፍል እንዲተላለፉ ይደረጋል::

3. ጥያቄ፣ በሥራ ላይ ያሉ መምህራን በጥናትና ምርምር ከተደረሰባቸው አዳዲስ ግኝቶች / የማስተማር ዘዴዎች ስልቶች፣ የዕቅድ አዘገጃጀት፣ የግምገማ ዓይነቶችና ስልቶች ወዘተ/ እንዲተዋወቁ አጫጭር ሴሚናሮች፣ ... ለምን እንዲካሄዱ አይደረገም?

## በት/ሚር ከሁለተኛ ደረጃ የቴክኒክና የሙያ መምህራን ትምህርት መምሪያ የተገኘ መልስ

የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና የሚከተሉት 3 ዋና ዋና ክፍሎች አሉት::

ሀ. የቅድመ ሥራ ሥልጠና /pre-service training/

ለ. የመግቢያ ሥልጠና / Induction / እና

ሐ. የሥራ ላይ ሥልጠና ወይም የሙያ ማሻሻያ /In-service Training / ናቸው:: የሥራ ላይ ሥልጠና ደግሞ በ3 ይከፈላል:: እነዚህም

ሐ.1 እየሠሩ ሥልጠና /on-the-job training /

ሐ.2 እንደገና ወይም ድጋሚ ሥልጠና / Re-training / እና

ሐ.3 የተከታታይ ትምህርት ወይም የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ስልጠና /continuing education or up-grading courses /ናቸው::

የሥራ ላይ ሥልጠና የመምህራንን አጥጋቢ ውጤት የመስጠት ችሎታን ያጎለምሳል፣ ፍላጎትን ያበረታታል፣ ተጨማሪ ዕውቀትን ያስገኛል፣ እንዲሁም የሙያ ዝንባሌን ያስፋል ተብሎ ይታመናል::

በሀገራችን ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ጠቀሜታዎች ለማግኘት እንዲቻል ከ1950ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በሥራ ላይ ላሉ መምህራን የተለያዩ የሥራ ላይ ሥልጠና ፕሮግራሞች ሲካሄዱ ቆይተዋል:: በአሁኑ ጊዜ የቀደሞውን ዓይነት ፕሮግራም ለማካሄድ ከማይቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ በመደበኛው የቅድመ ሥራ ሥልጠና ፕሮግራም ለትምህርቱ ሥርዓት የሚያስፈልጉ መምህራን ተሟልተው ስለማይ መረቁና ከዚህም የተነሳ ያልሰለጠኑ ወይም የትምህርት ደረጃቸው ለሚመደቡበት ክፍል የማይመጥን መምህራን ስለሚቀጠሩ፣ የሚዘጋጁት ፕሮግራሞች እነዚህን መምህራን በትምህርት ደረጃና በሙያ ብቁ ለማድረግ ስለሚውሉ ነው::

በዚህ ረገድ ከ1969-1976 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ከ10 ቀን እስከ 6 ክረምት ለሚሆን ጊዜ የተለያዩ የሙያ ማሻሻያና የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞች ታቅደው በርካታ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ተካፍለዋል:: የሚከተለው ሠንጠረዥ ይህንን ያሳያል::

የአጭር ጊዜ የሙያ ማሻሻያና የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም የተሰጣቸው የትምህርት ባለሙያዎች ብዛት በየዓመቱ /1969-1976/

| ዓመተ ምህረት | የሠለጠኑ መምህራን ብዛት |
|---|---|
| 1969 | 592 |
| 1970 | 1059 |
| 1971 | 1428 |
| 1972 | 2037 |
| 1973 | 2415 |
| 1974 | 2711 |
| 1975 | 2806 |
| 1976 | 2667 |

በተጨማሪም የወደፊቱን ሁኔታ በተመለከተ ትምህርት ሚኒስቴር በአሁኑ ወቅት የመምህራን ትምህርትና የትምህርት ባለሙያዎች ሥልጠና ዋና መምሪያ በሚል ስያሜ የከፈተው አዲስ የሥራ ክፍል ለመምህራን አጭር ሴሚናሮችና ወርክሾፖች በማዘጋጀት በትምህርት ጥናትና ምርምር ከተደረሰባቸው አዳዲስ ግኝቶች ጋር የማስተዋወቁን ተግባር ዋነኛ ሥራው አድርጎ የሚይዝ ነው::

4. ጥያቄ፤ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በተለይም የማስተማሪያ መጽሐፍት ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ለምን እንዲመጣጠን አይደረግም?

በት/ሚር ከትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የተገኘ መልስ

ምንም እንኳ በመንግሥት ት/ቤቶች የመማሪያ መጽሐፍት በየዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለተማሪዎች በትውስት ተሰጥተው በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚሰበሰቡ ቢሆንም፤ አሠራሩ በየዘመኑ የሚታተሙትን መጽሐፍት በቁጠባ

እንዲሠራባቸው አድርጓል:: የድርጅቱ ግብ /target / ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት በየክፍል ደረጃው አንድ መጽሐፍ ለሁለት ተማሪዎች በትውስት ለማዳረስ ነው:: የየትምህርቱን ዓይነት መጽሐፍት ለእያንዳንዱ ተማሪ በነፍስ ወከፍ ለማዳረስ ያለው ችግር፣ በርካታ አዳዲስ ት/ቤቶች በየዓመቱ መከፈታቸውና ነባሮቹም በቦታ ጥበት የተነሳ በፈረቃ ለማስተማር መገደዳቸው የተማሪዎች ቁጥር በጥቂት ዓመታት ውስጥ በሁለትና በሶስት ዕጥፍ እንዲያድግ ሲያደርግ ለመማሪያ መጽሐፍት ዝግጅትና ሕትመት መንግሥት ከሚመድበው በጀት ጋር ተመጣጣኝ ዕድገት አለማሳየቱ፣ በአገር ውስጥ ለመጽሐፍት ሕትመት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች ለምሳሌ፣ ወረቀትና ኬሚካል በሚፈለገው መጠን አለመገኘታቸው፣ እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች ከውጭ ለመግዛት ደግሞ የውጭ ምንዛሪ እጥረት መኖሩ ነው:: ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ ብሔራዊ ፈተና ለሚሰጥባቸው ክፍሎች ማለትም ለ6ኛ፣ 8ኛና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች እያንዳንዱ ተማሪ በየትምህርት ዓይነቱ የተዘጋጀውን መጽሐፍ በነፍስ ወከፍ እንዲያገኝ ለማድረግ እየሞከረ ነው::